# ከህዝብ ስሜት መማር የተሳነው ተቃዋሚ የፖለቲካ ጎራ

**ዳዊት አጥናፉ** 11/12/12

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ህልፈት ተከትሎ የተለያዩ የታላላቅ አገራት መሪዎችና ዓለም አቀፍ ድርጅት ኃላፊዎች ባወጧቸው መግለጫዎች መለስ ለአገራቸው፣ ለአፍሪካና ለተቀረው የዓለም ክፍል ሰላምና እድገት ውጤታማ ተግባር መፈፀማቸውን በመግለፅ ለስራቸው እውቅና ሰጥተዋል፡፡

የመለስ ህልፈት የሚጎዳው ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ጭምር መሆኑንም በይፋ ገልፀዋል፡፡ ይህ መለስ የተከሉትና መላው ህይወታቸውን መስዋእት ያደረጉለት ራእይ በተተኪዎቹ የአገሪቱ መሪዎችም ተጠናክሮ እንዲቀጥል በአፅንኦት መጠየቃቸውም መግለጫዎቹን በወቅቱ የተከታተልን የምናስታውሰው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለመለስ ስኬታማ ወጤት የሰጠው እውቅና በምንም የሚለካ አይደለም፡፡

ይህ በኢትዮጵያዊያንና በዓለም አገራት መሪዎች የተንፀባረቀው አድናቆትና እውቅና የመነጨው ከምንም ሳይሆን ፍፁም በሆነ ጨለማ ውስጥ ተውጣ ለዝንት ዓለም የኖረችውን ኢትዮጵያ በእድገት ብርሃን ለመሙላት የሚያስችላትን ብሩህ የሆነ ራእይ ያመላከቱ እንደዚሁም በአፍሪካ አገራት በተለይም በአፍሪካ ቀንድ ለብዙ ዓመታት የቆዩ ግጭቶች በሰላም እንዲጠናቀቁ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ መሪ በመሆናቸው ነው፡፡

ያም ሆኖ የስልጣን ጥም የሚያንገበግባቸው ጥቂት የአገራችን ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ኢትዮጵያዊያንም ሆኑ የተለያዩ የዓለም አገራት መሪዎችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ኃላፊዎች የመሰከሩትን የመለስ ብሩህ ራእይ ለማጣጣል ቀደም ሲል ሞክረውት የነበረውን ሰሚ ያጣውን ተስፋ ቢስ ዘመቻ ሰሞኑንም ጀምረውታል፡፡

ፅንፈኞቹ የፖለቲካ ቡድኖችም ሆኑ በኢትዮጵያ ኒዮ ሊበራል የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ስርዓትን ለመገንባት የሚውተረተሩት አካላት የተቀናጀ በሚመስል መልኩ ባካሄዱት ዘመቻ በህዝቡ ውስጥ አመፅ እንዲነሳ ሰብከዋል፤ የሌለ ታሪክ በመፈብረክ በገገርው ፓርቲ ኢህአዴግ ውስጥ የስልጣን ሽኩቻ ተፈጥሯል የሚል ፕሮፓጋንዳ ነዝተዋል፡፡

የተለያዩ የአገራችን ዜጎች በተለያዩ ወቅቶች በሰጧቸው አስተያየቶች እንደገለፁት የእንደዚህ ዓይነቶቹ ተግባራት ዓላማ በመንግስትና ህዝብ መካከል ጥርጣሬ እንዲፈጠር ብሎም

በመንግስት ላይ አግባብ ያልሆነ ተቃውሞ እንዲያነሳ እንደዚሁም በህዝቡ ውስጥ ተስፋ የመቁረጥ ስሜትን በማነሳሳት ስርዓት አልበኝነት እንዲነግስ ማድረግ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

እነዚህ አካላት መለስ ታመሙ ከተባለበት ጊዜ አንስቶ ለስልጣን በመቋመጥ ኢትዮጵያ በብጥብጥና ሁከት የእሳት ማእበል እንድትናጥ አልመዋል፤ የበኩላቸውን መፍጨርጨርም አድርገዋል፡፡ ሰሞኑንም በአንዳንድ የተቃዋሚ ድረ-ገፆችና ጥቂት የግል ጋዜጦች ላይ እየተሰሙ የሚገኙት የጥላቻና በሬ ወለድ አስተያየቶች ፍፁም ሀሰትና ተራ የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ በመሆናቸው ማንም ጆሮ አይሰጣቸውም፡፡

ምክንያቱም ፖለቲከኛ ተብዬዎቹ ማስተጋባት የጀመሩት አስተያየት ፍፁም ተራና በቅጥፈት የተሞላ ከመሆኑም በተጨማሪ በመለስ የአመራር ዘመን አገሪቱ ያሳየችው ለውጥ የሚታይና የሚጨበጥ በመሆኑ በምንም ዓይነት ሌላ ጭፍን የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ሊስተባበል የሚችል አይደለም፡፡ በአሁኑ ወቅት በእነዚህ አካላት የተጀመረው ዘመቻ በመለስ የአመራር ዘመን በአገራችን የታየውን ተጨባጭ ለውጥ በማጣጣል ተራ የፖለቲካ ትርፍ ማሳደድ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጭምር ልዩ በሆነ መልካም ገፅታ መታየት የጀመረችው በአገሪቱ አዲስ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓት ተግባራዊ በሆነበት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ጊዜ ውስጥ መሆኑ ማንም ሊያስተባብለው የማይችለው እውነት ነው፡፡

አገሪቱ ለዚህ የበቃችው ደግሞ በአገሪቱ የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ መላው ዜጋ ቁልፍ ተዋናይና የአገሪቱ ኃብት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆን ያስቻለ ህገ መንግስት በህዝቦች ቀጥታ ተሳትፎ ተቀርፆ ስራ ላይ በመዋሉ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ያቀረቡ የአገር ውስጥም ሆኑ የውጭ አገራት ምሁራን በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደገለፁት የአገሪቱ ህገ መንግስት ከዘመን ዘመን እየተሻገረ ይመጣ በነበረው የፖለቲካ ጭቆና ሳቢያ ለመበታተን ቅርብ የሆነ አደጋ ውስጥ ወድቆ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነቱን አጠናክሮ በጋራ መኖር የጀመረው በህገ መንግስቱ መሰረት በተዋቀረው ፌደራላዊ የፖለቲካ ስርዓት አማካኝነት ነው፡፡

ይህ በመላው የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተች አንዲት ኢትዮጵያን ለመፍጠር ያበቃ ከመሆኑም በተጨማሪ አገሪቱ ለዘመናት የምትታወቅበትን ድህነት ለመዋጋት የሚያስችል የህዝቦች መተማመንንና የጋራ ራእይን ለመፍጠር አስችሏል፤ አገሪቱ ወደአዲስ ምእራፍ እንድትሸጋገር መንገዱን ጠርጓል፡፡

በአጠቃላይ ስርዓቱ ዜጎች ልብ ውስጥ ጠንካራ መተማመንና አገራዊ ስሜት እንደዚሁም ብሄራዊ መግባባትን በማምጣት ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚያግዝ የጋራ ህብረትን እውን አድርጓል፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ እየታየ ያለው በብርሃን የተሞላ ተስፋና መልካም ሁኔታ እውን የሆነው የመላው የአገሪቱ ህዝቦች ዘመናትን ያስቆጠረ ትግልን ተከትሎ ቢሆንም ይህ ህዝብ በተለያየ መልኩ ያካሄደው ትግል ለዚህ ፍሬ እንዲበቃ ከማስቻል አንፃር ግን ከማንም የላቀ መጠን ቁልፍ ሚና የተጫወተው ዛሬ አገሪቱን በመምራት ላይ የሚገኘው ኢህአዴግ ስለመሆኑ ከማንም ሊሰወር አይችልም፡፡

ኢትዮጵያ ወደአዲስ የእድገትና ለውጥ ምእራፍ መሸጋገር የጀመረችው አገሪቱን የሚመራው ድርጅት ግልፅና የላቀ የለውጥ ራዕይ በመቅረፁ፣ ይህንንም ወደተግባር ለመለወጥ ህዝባዊ አመኔታንና ይሁንታን በመቸሩም ጭምር መሆኑን ለማስተባበል መሞከር ከጤነኛ አእምሮ የሚመነጭ አይመስለኝም፡፡

ከዚሁ ጋርም የአገሪቱ መሪዎች አገሪቱ ያላትን እጅግ አነስተኛ ኃብት እንደዚሁም ከተለያዩ አካላት የሚገኘውን የልማት ድጋፍና ብድር ለታለመላቸው ስራዎች በተገቢው መንገድ በማዋላቸው መሆኑን ብዙዎች ይናገራሉ፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መንግስት ድህነትን ለማሸነፍ የያዘው እጅግ ጠንካራ ቁርጠኝነትና ግልፅ የሆነ ራዕይ ለስኬቱ ዋነኛው ምክንያት እንደሆነ በብዙዎች ተመስክሯል፡፡

ኢህአዴግ ሲጠቀስ ደግሞ የድርጅቱ መሪዎች በተለይም የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ግንባር ቀደም ናቸው የሚል እምነት አለኝ፡፡ የዛሬዋ ኢትዮጵያ እንድትፈጠር ምክንያት በሆኑት ሁለንተናዊ አገራዊ የልማት ራእዮች ውስጥ የመሪው መለስ ዜናዊ አሻራ በጉልህ የሚታይ መሆኑን ከአገሪቱ ዜጎች ባለፈ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጭምር ተመስክሯል፡፡

የደርግ ስርዓት እስካበቃበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያዊያን በከፋ ድህነት ውስጥ ነበሩ፡፡ የአገሪቱ ልዩ መታወቂያም ድህነት፣ ርሃብና ድርቅ ብቻ እንደነበር ሁላችንም የምናውቀው ሀቅ ነው፡፡

የአገሪቱን አንገብጋቢ ችግሮች የተገነዘበው የኢህአዴግ መንግስት በቅድሚያ ከ80 በመቶ በላይ የሆነውን ህዝብ የሚይዘውን አርሶ አደር የስቃይ ህይወት ለመለወጥ የወሰዳቸው እርምጃዎች የአርሶአደሩን ህይወት በእጅጉ ለውጠውታል፡፡ ከዚህ በፊት ለእለት ጉርሱ እንኳ ይጨነቅ የነበረው የአገራችን አርሶ አደር ዛሬ ምርታማነቱ በብዙ እጥፍ ጨምሮ ምርቶቹን ለገበያ በማቅረብ ኃብት ለማካበት ችሏል፡፡

የእነ መለስ የግብርና ልማት ስትራቴጂ የአርሶ አደሩን ህይወት ከመቀየር ባለፈ አገሪቱ በምግብ ራሷን የምትችልበትን ተስፋ ሰጪ መንገድንም አጎናፅፏል፡፡ የተለያዩ እርዳታ ሰጪ አገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በተለያዩ ጊዜያት ባወጧቸው ሪፖርቶች በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎች በርሃብ ህይወታቸው እንዳያልፍ የሚያስችል አቅም መፈጠሩን አረጋግጠዋል፡፡ አገሪቱ የተፈጥሮ አደጋን ተከትሎ ለሚከሰት የምግብ እጥረት ችግሮች በራሷ አቅም የምግብ እህል በማቅረብ ምላሽ በመስጠት የፈጠረችውን አቅም በተግባር ማረጋገጧንም እነዚሁ አካላት መስክረዋል፡፡

ዛሬ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ትምህርት ቤቶች ተስፋፍተዋል፡፡ በዚህም አማካኝነት በተለይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ መቶ በመቶ ደርሷል የሚባልበት ደረጃ ላይ መድረስ ተችሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን የሚከታተሉት ህፃናት ቁጥር በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሆኗል፡፡

በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ረገድም በአሁኑ ወቅት የሚታየው እመርታ አገሪቱ በታሪኳ አይታው የማያውቀው ዓይነት ነው፡፡ የአገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአሁኑ ወቅት ብቻ ከሁለት መቶ ሺህ በላይ ተማሪዎችን በማስተናገድ ላይ ናቸው፡፡

በጤናው ዘርፍ ዜጎች እያዩት ያለው ለውጥን በእጅጉ የሚበረታታ ነው፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን የገጠሪቱ ህዝብ የጤና አገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ ተሻሽሏል፡፡ ዛሬ ሁሉም በሚኖርበት አቅራቢያ የጤና ጣቢያና የጤና ኬላ ተገንብቶለታል፡፡ ህዝቡም አስፈላጊ የሆኑትን የጤና ባለሙያዎችንም በየደጁ ያገኛል፡፡ በዚህም አማካኝነት በጤና አገልግሎት እጦት ሳቢያ ህይወታቸው የሚያልፈው ዜጎች ቁጥር እዚህ ግባ የማይባልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

የህዝቡ የጤና አጠባበቅ ሁኔታም በእጅጉ በመሻሻል ላይ ይገኛል፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር አመራር ዘመን ባለፉት 20 ዓመታት የተከናወኑት ተግባራት አገሪቱ በዜናው ዘርፍ የምእተ ዓመቱን የልማት ግብ ለማሳካት እንድትቃረብ እንደሚያስችላትም እየተነገረ ነው፡፡

በአቶ መለስ አመራር አገሪቱን በማገልገል ላይ የሚገኘው መንግስት በተለይ በከተሞች አካባቢ ያለውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመቅረፍ የወሰዳቸው እርምጃዎችም አያሌዎችን የቤት ባለቤት አድርጓል፡፡ ከዚህም ባሻገር ወጣቶችን በተለያዩ የጥቃቅንና አነስተኛ የሙያ ዘርፎች በማሰልጠን፣ አስፈላጊውን የመስሪያ ቦታና የስራ ማስካሄጃ ብድር በማቅረብ እንደዚሁም የገበያ ትስስር በመፍጠር የዜጎችን የስራ እድልና የገቢ መጠን ማጠናከር ተችሏል፡፡

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በመላው አገሪቱ የተገነቡት መንገዶች የአገሪቱን የልማት አጋሮች ጭምር በእጅጉ ያስደመሙ የተሳኩ የመለስ ዜናዊ የስራ ውጤቶች ናቸው፡፡

ከዚህም ባሻገር የአገሪቱን የኃይል አቅም ለማጠናከር ባለፉት ዓመታት የተወሰዱት እርምጃዎችና የታቀዱት ተግባራት አገሪቱን በአካባቢው አገራት የሚያስጠራ እንደሚሆን ይገመታል፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለው ሰላምና መረጋጋት እጅግ አስተማማኝ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አገሪቱ በዓለም ፈጣን የሚባል ኢኮኖሚያዊ እድገትን በማስመዝገብ መላውን ዓለም በማስደመም ላይ ትገኛለች፡፡

ከፊታችን ገና ብዙ ተግባራት የሚጠብቁን ቢሆንም ከ20 ዓመት በፊት ምንም ያልነበረው ብሄራዊ ኃብት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ እድገት እያመጣ ጠንካራ የሚባል ደረጃን ተቀዳጅቷል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ሚሊዮኖች ከድህነት ወጥተዋል፡፡ የአገሪቱ የድህነት መጠንም በከፍተኛ መጠን ማሽቆልቆል ጀምሯል፡፡

ይህ የአገሪቱ ለውጥ በዓለም በግዙፍነታቸው የሚጠሩትን ጨምሮ በርካታ የውጭ አገራት ኩባንያዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ የሚያስችላቸውን መተማመን ፈጥሯል፡፡

በአጠቃላይ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናት በቁማቸው ያንቀላፉ የነበሩ ነፍሶች የተነቃቁት፣ ሳይታሰሩ ታስረው የነበሩ ሚሊዮን እጆች በማያቋርጥ ስራ የተጠመዱት፣ በራእይ እጦት ሳቢያ ጥቅም ላይ ሳይውሉ የኖሩ የአገሪቱ የተፈጥሮ ኃብቶች የእድገት ሞተር ለመሆን የበቁት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

ይህ ለውጥ ሊመጣ የቻለው ኢትዮጵያዊያን በተለይ ካለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ጀምሮ በተለየ የፖለቲካና ኢኮኖሚ መዋቅር ውስጥ መኖር በመጀመራቸው መሆኑን ብዙዎች ይመሰክራሉ፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት አገሪቱንና ዜጎቿን ለዚህ የተለየ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓት ያደላት ደግሞ ከአገር አልፎ ዓለም አቀፍ የፖለቲካና ማህበረሰባዊ ሳይንስ ምሁራን ሳይቀሩ በመሰከሩለት ህገ መንግስት አማካኝነት ነው፡፡

ይህ ህገ መንግስት አገሪቱ ከተመራችባቸው ቀደምት ህገ መንግስቶች የሚለይበት ዋናው ቁም ነገር ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የአገሪቱ ባለቤቶች፣ አድራጊና ፈራጆች እንዲሆኑ ሙሉ መብት መስጠቱ ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያዊያ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓት ቀደምት የአገሪቱ ገዢዎች አፍነውትና ረግጠውት ለኖሩት የዘመናት የህዝቦች የመብት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ሰጥቷል፡፡

ይህንንም መብቶቻቸውን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉበትን የፌዴራላዊ ስርዓት እንዲገነቡ፣ በዚህም አማካኝነት የአገሪቱ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር መቻላቸውና ከአገሪቱ ኃብትም ፍትሃዊ ተጋሪነታቸው እንዲረጋገጥ አድርጓል፡፡

እነዚህ የህገ መንግስቱ ዓይነተኛ ገፅታዎች በአገሪቱ ታይቶ የማይታወቅ ሰላምና መረጋጋትን እንደዚሁም የህዝብን ህይወት ሊያሻሽል የሚችል ኢኮኖሚያዊ እድገትን አምጥተዋል፣ ለዘመናት በጎሪጥ ሲተያይ በኖረው ህዝብ መካከልም መተማመንንና አንድነትን ፈጥሯል፡፡

ይህንን በዓይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ እውነት አለመቀበል በማንም ጤነኛ አእምሮ እይታ ከፍተኛ ክህደት ነው፡፡

ጥቂት የተቃዋሚው ክፍል ግለሰቦች ሰሞኑን እየሰጡት ያለው አስተያየት በምንም መልኩ ሊስተባበልና ሊደበቅ የማይችል ፊጦ የሚታይ እውነትን ለማድበስበስ የሚደረግ ትርጉም አልባ ጥረት ነው፡፡ ለአገሪቱ አድገትና የወደፊት ተስፋ ኃይል የሆነውን ተጨባጩን የአገራችንን የለውጥ ጎዳና በማጣጣል የህዝብን ድጋፍ አገኛለሁ፣ የፖለቲካ ስልጣንንም እቀዳጃለሁ ብሎ ማሰብ ፍፁም ድንቁርና ነው፡፡ በተለይ ተምረናል ከሚሉት የአገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ሰዎች የዚህ ዓይነቱ አስተያየት ሲደመጥ በእጅጉ ያስተዛዝባል፡፡

የአገራችን ተቃዋሚዎች የዚህ ዓይነቱ የትግል መንገድ ከመለስ ህልፈት ጋር ተያይዞ የመጣ ሳይሆን ላለፉት 20 ዓመታት የኖረ ነው፡፡

መድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲን ለመገንባት ጥረት በሚያደርጉ አገራት ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚዎች ስልጣን በያዘው መንግስታቸው ላይ ገንቢ ትችቶችን በመሰንዘርና ለህዝብና አገራቸው ይበጃል የሚሉትንና በተገቢ ጥናት የተደገፈ አማራጭ ፖሊሲ በማቅረብ ለመንግስታቸውና ህዝባቸው የሚጠበቅባቸውን ድጋፍ ሲያደርጉ ይታያል፡፡

የኛዎቹ ተቃዋሚዎች ተግባር ግን ከዚህ ፍፁም የተቃረነ ነው፡፡ ዘውትር የመንግስትን ስራዎች ከማጣጣልና በህዝብ ልብ ውስጥ ጥርጣሬንና ተስፋ መቁረጥን ለመትከል ከመጣር ውጭ አንድም ገንቢ ሚና ታይቶባቸው አያውቅም፡፡ የአገራችን ተቃዋሚዎች ተግባር ከአገር ልጅ ቀርቶ ከባእዳን እንኳ የማይጠበቅ ሁሌም በጥፋት የተሞላ ነው፡፡

ለህዝብና አገር እንቆረቆራለን እያሉ ሁሌም ተጠምደው የሚገኙበት ምግባር ግን ህዝብንና አገርን ለጥፋትና ለውድቀት የሚዳርግ ነው፡፡ ይህም እውነታ ተቃዋሚዎቻችን የዘውትር ህልምና ቅዥት ስልጣን ብቻ መሆኑን ያለምንም ማወላዳት ያሳያል፡፡

ላለፉት 20 ዓመታት የተሞከረው ይህ ጥፋት ብቻ የተሞላበት የትግል ስልት የማይሰራ መሆኑን ህዝቡ በተግባር እያሳየ ባለበት በአሁኑ ወቅት ተቃዋሚዎቻችን በዚሁ መስመራቸው ተጠምደው መገኘታቸው እኔን ብቻ ሳይሆን ብዙዎችን ግራ እንደሚያጋባ በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ፡፡

የዚህች አገር ህዝብ ፍላጎት ገሃድ ከወጣ ቆይቷል፡፡ ህዝባችን የመለስ ህልፈት ሰሞንም ሆነ ከዚያ በፊት እንደዚሁም በአሁኑ ወቅት በተለያዩ አጋጣሚዎች ያንፀባረቀው እውነት አገሪቱን እየመራ ላለው መንግስት እውቅናንና ድጋፍን የሚሰጥ ነው፡፡

ህዝቡ የተቃዋሚዎች መንገድ የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን ከአገርና ህዝብ ይልቅ የግል የፖለቲካና የስልጣን ፍላጎት ያደረ መሆኑን በተግባር አሳይቷል፡፡ ጽንፈኝነትንና ጥፋትን ለማስተናገድ መቼም ቢሆን ጊዜ እንደሌለውም በሚገባና ግልፅ ባለ መልኩ አሳይቷል፡፡ የማንም ፖለቲካ ዓላማ መጠቀሚያ እንደማይሆንም ድምፁን ከፍ አድርጐ አውጇል፡፡

ይህንን የህዝብ ስሜት መረዳት አለመቻል በእውነቱ ጤነኝነት አይመስለኝም፡፡ በአገሪቱ የተተከለው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓት የህዝብ ይሁንታ ያለው ብቻ ሳይሆን አገሪቱንም ለእድገት ያበቃ መሆኑን ላለመቀበል መዳዳት ትክክለኛ የፖለቲካ ትግል ስልት አይደለም፡፡ ዘውትር መንግስትንና ተግባራቱን ማጣጣልም የትክክለኛ ተቃዋሚ ፖለቲከኛ መንገድ አይደለም፡፡